M11/1/A1AMH/SP2/AMH/TZ0/XX

22110016

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2**

Monday 16 May 2011 (morning)
Lundi 16 mai 2011 (matin)
Lunes 16 de mayo de 2011 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.
- Vous n'êtes pas autorisé(e) à amener des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d'examen.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.
- No se permite traer a la sala de examen copias de las obras estudiadas.


© International Baccalaureate Organization 2011

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ)። መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት። በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል። በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም።*

**ድራማ**

1. ገፀባህርያቱን ልዩና የማይረሱ አድርጎ ማቅረቡ የፀሀፌ ተውኔቱ ዋነኛ ተግባር ነው። ይህንን ሃሳብ ባጠናሃቸው ሁለት ድራማዎች ምሳሌነት ግለጽ።

2. ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ሞት በስራዎቹ እንደምን እንደቀረበ አሳይ።

**ረጅም ልቦለድ**

3. አንባብያን ከሚያነቡዋቸው ልቦለዶች ገፀባህርያት ጋር ሲያፈቅሩ፣ ሲጠሉና ሲፈሩ ይፈልጋሉ። ደራስያን እንዴት የአንባቢዎቻቸውን ስሜት በገፀባህሪያቶቻቸው አማካኝነት እንደሚይዙ ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ግለጽ።

4. ያለግጭት የአንድ ልቦለድ ታሪክ ማራኪ ሊሆን አይችልም፤ የሚያስተምረው ነገር አይኖርምና። ግጭት እንደምን አንባቢውን እንደሚያስተምር ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ አስረዳ።

**ስነግጥም**

5. የስነግጥም መሰረቱ ከተለመደው እውነታን መግለጫ የቋንቋ አጠቃቀም ወጣ ያለ አቀራረብ መከተሉ ነው። ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በመመርኮዝ ግለጽ።

6. ስነግጥም የሰው ልጆች ቋንቋ ከይዘቱ ባሻገር ውበት ባለው መንገድ የሚቀርብበት ነው። ይህንን ሀሳብ ያነበብካቸውን የተለያዩ ገጣምያን ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በመጥቀስ አብራራ።

**ዝርው (ከረጅምና አጭር ልቦለድ ሌላ)**

7. ማንኛውም ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) በአንድ ሃሳብ ወይም ጉዳይ ላይ ከማተኮሩ በተጨማሪ ሃሳቡ የቀረበበት መንገድ እጅግ ጠቃሚና ዋነኛ ነው። ይህም የሚሆነው ጽሁፉ የደራሲውን አመለካከት የሚያንፀባርቁ ነጥቦች ይኖሩታልና ነው። ያጠናሃቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ የሀሳቡን ጠቀሜታ አስረዳ።

8. የማንኛውም ዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) መግቢያ የሚስብና የሚይዝ ሆኖ አንባቢው ጽሁፉን ጨርሶ እንዲያነብ የሚገፋፋ መሆን አለበት። ያነበብካቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ሃሳቡን አስረዳ።



https://xtremepape.rs/

**አጭር ልቦለድ**

**9.** በአጭር ልቦለድ አንዳንድ ገፀባህርያት ከሌሎቹ ይበልጥ ተአማኒ ናቸው። ባጠናሃቸው ስራዎች አንድ በከፍተኛ ደረጃ ተአማኒ እንዲሁም ሌላ በዝቅተኛ ደረጃ ተአማኒ ገፀባህሪያት በማወዳደር የሃሳቡን ትክክለኛነት አስረዳ።

**10.** ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት አጭር ልቦለዶች ውስጥ ዋነኛው የልቦለዶቹ ሐሳብ እንዴት እንደቀረበ ግለጽ።

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

**11.** ስነጽሁፍ ከግል ገጠመኞቻችን አልፈን አዲስ አለም እንድንተዋወቅ የሚያደርገን ነው። ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር ይህንን ሀሳብ አስረዳ።

**12.** በርካታ የስነጽሁፍ ስራዎች መናፈቅንና በጉጉት መጠበቅን በስራዎቻቸው በዋናነት ያቀርባሉ። መናፈቅና በጉጉት መጠበቅ ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች እንደምን እንደቀረበ አብራራ።

**13.** የስነጽሁፍ ስራዎች አንዱና ዋነኛው ተግባር አንባቢው በህሊናው ልዩ ስፍራ እንዲደርስ ማድረግ ነው። ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ይዘትና ስልት በመጥቀስ የዚህን ሃሳብ ትክክለኛነት አስረዳ።

**14.** ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ የቤተሰብ ግንኙነት እንደምን እንደቀረበ ግለጽ።

---



https://xtremepape.rs/